Legal Aid Society
OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MAKING JUSTICE REAL

# የቤተዘመድ ሁካታ (Domestic Violence)
# (ጁላይ 27፣ 2022 ተሻሻለ)


የቤተዘመድ ሁከታ/ብጥብጥ (domestic violence) ምን ማለት ነው?

አደጋ ሲያጋጥም ከማን ጋር ነው መገናኘት ያለብኝ?

የሲቪል መከላከያ ትእዛዞች

- የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ምን ማለት ነው?
- በሲቪል መከላከያ ትእዛዝና በግዚያዊ መከላከያ ትእዛዝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ማነው የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችለው?
- የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ የሚያደርገው ምንድነው?
- በኮቪድ-19 (COVID-19) አደገኛ ወቅት እንዴት ነው የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲደረግልኝ መጠየቅ የምችለው?

ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዞች

- እንዴት ነው ይህንን ግዜያዊ የመከለከያ ትእዛዝ ማግኘት የምችለው?
- ከስራ ሰዓታት ውጪ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ቢያስፈልገኝስ?
- የተሰጠኝ ግዜያዊ የመከለከያ ትእዛዝ እስከ ስንት ግዜ ይቆያል?

መርሃ ግብር (Scheduling) ማውጣትና ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች

- የሲቪል መከላከያ ትእዛዜን ለመቀበል መቼ ነው ፍርድ ቤት የምሄደው?
- ጉዳዬ በሚሰማበት ወቅት፡ ችሎቱ በቨርቿል ከሆነ ምንድነው የሚሆነው?
- ለማረጋገጥ ሲደውሉ አንድ ጽሃፊ መረጃዎን እንዲሰጡ ይጠይቃል። ነገሩን የሚያስማም ሰው ሲገኝ ፤ ፍርድ ቤት ራሱ በመደወል ዳኛው ጉዳዮን ለመስማት ዝግጁ ሲሆን ይደውልሎታል። ከስልኩ አጠገብ መሆንን አይዘንጉ፤ በዛው ቀን ከከሰዓት በኋላ፤ ከ5:00 ሰዓት በፊት ከፍርድ ቤት እንደሚደወልሎት ይወቁ።
- ፍርድ ቤቱ ተዘግቶ እያለ፤ የሲቪልም ሆነ የግዜያዊ የመከላከል ትእዛዞቼ ግዜያቸው ቢያልፍስ?
- በወቅቱ ያለኝን ግዚያዊ ወይም የሲቪል መከላከያ ትእዛዞችን ማራዝም ብፈልግ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?

[የህግ እርዳታ](#)

[ምክርና ድጋፍ (Counseling and Support)](#)

- [ለምክርና ለድጋፍ ወይም የደህንነት ዕቅድ ለማውጣት ከማን ጋር ልገናኝ?](#)

[የልጅ አሳዳጊነት መብት (Custody)](#)

- [የልጅ አሳዳጊ መብት እንዲሰጠኝ እንዴት ነው ጥያቄ ማቅረብ የምችለው፤ ባለኝ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ ላቀርብ እችላለሁን?](#)
- [በግዚያዊ የመከላከያ ትእዛዝ በኩል ያገኘሁት የልጅ ማሳደግ መብት አለኝ። ይህ ትእዛዝ እንዲቆይልኝ ወይም እንዲራዘምልኝ አዲስ የልጅ ማሳደግያ ፋይል መክፈት አለብኝን ?](#)
- [ሌላኛው ወላጅ በልጃችን ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ ነው የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ልጃችን፤ ያኛውን ወላጅ ለብቻው ሂዶ ሲያይ ደህንነቱ ይጠበቃል የሚል ስሜት የለኝም። ምን ማድረግ አለብኝ ?](#)
- [በእኔ ላይ ግፍ የሚፈጽመው ሰው ግፍ ፈጽሞብኛል፤ ወይም እያስፈራራኝ ነው። በአሁኑ ወቅት ልጃችንን እንዲጎበኘ ማድረግ ከልጃችን ደህንነት አንጻርጋር አመዛዝኜ ሳየው ትክክል አይደለም የሚል ስሜት አለኝ። ምን ማድረግ አለብኝ?](#)
- [ያለኝ ወቅታዊ የሲቪል መከለከያ ትእዛዝና የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ሁለቱም በልጅና በወላጅ መካከል ለሚደረጉ ጉብኝቶች መቀባበሉ ታዛቢ ባለበት የጉብኝት ማእከል እንዲሆን ነው የሚያዙት ስለዚህ ምን ማድረግ አለብኝ?](#)
- [ያለኝ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝና የአሳዳጊ መብት ትእዛዝ የሚጠይቁት በአንዱ ወገንና በሌላው ወገን የሚደርግ የልጆች ቅብብሎሽ  ታዛቢ ባለበት በጉብኝት ማእከሉ ብቻ እንዲሆን የሚያዝ ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?](#)

[ፍቺ (Divorce)](#)

- [ባለቤቴ ገንዘባችንን የሚቆጣጠር እርሱ ነው። እና እጄን በገንዘብ ጉዳይ ውስጥ እንዳልከት ከልክሎኛል። ያሉኝ አማራጮች ምንድናቸው ?](#)

[መኖርያ ቤት (Housing)](#)

- [ጉዳት የሚያደርስብኝን ሰው ጥዬ መውጣት አለብኝ። የቤተዘመድ ግፍ የደረሰባቸው ሰዎች የሚቆዩባቸው መጠግያ ቦታዎች አሁንም በዚህ በወረርሽኝ አደጋ ግዜ ክፍት ናቸውን ?](#)
- [ከ የወንጄል ሰለባዎች እርዳታ ፕሮግራም (Crime Victims Compensation Program) እርዳታ ማግኘት እችላለሁን?](#)
- [በቤት ውላችን ውስጥ ግፍ ፈጳሚዬና እኔ ተዘርዝረናል። ከግፍ ፈጳሚዬ ጋር አንድ ቤት መኖር ስለአም አይሰማኝም።  በዚህ ባለንበት የወረርሽን ወቅት ከቤት እንዲወጣልኝ ላስገድደው እችላለሁን?](#)
- [ይህንን ቦታ ለቅቄ መውጣት አለብኝ ምክንያቱም ግፍ ፈጳሚው የት እንደምኖር አሁን አውቋል። ያደረኩትን የቤት ኪራይ ውል ማፍረስ እችላለሁን?](#)
- [በዚህ የወረርሽን በሽታ ወቅት፡ ግፍ ፈጳሚዬ ከቤት አስወጣሻለሁ እያለ እያስፈራራኝ ነው። የምሄድበት ቦታ የለኝም። የቤት ኪራይ በመክፈል ረገድ እየተጋገዝኩ የነበርኩ ብሆንም፤ የቤት ኪራይ ውል ውስጥ የለሁም። ከቤት ሊያስወጣኝ ይችላልን?](#)

ግፍ ፈጻሚዬ የሴክሽን ስምንት (Section 8) ቤቶችን ለማግኘት ኩፖን አለው። እኔም በኩፖኑ ውስጥ አለሁ።ግን የቤቱ የበላይ ሃላፊ (Head of Household) አይደለሁም። ከሱ ጋር ለመገላገል ስወስን ኩፖኑን ልጠቀምበት እችላለሁን?

ህዝባዊ ጠቀሜታዎች

ግፍ ፈጻሚዬ ለቤተሰባችን ገንዘባዊ እርዳታ የሚያድረግ ነበር። እኔ ግን ከዛ ሁኔታ መላቀቅ ስለነበረብኝ ወጣሁ። በዚህ በወረርሽኝ ግዜ፤ ለምግብና ለአንዳንድ ቁሳቁሶች መግዥያ ላገኘው የምችል እርዳታ አለን?

የስናፕ SNAP ና ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ጠቀሚታዬን ለማግኘት ምን ያህል ግዜ መጠበቅ አለብኝ?

የስናፕ SNAP ወይም የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ጠቀሜታዎችን ለማግኘት በማመልከት ረገድ ችግር ካጋጠመኝ የት ነው የምደውለው?

በኔ ላይ ግፍ የሚሰራው ሰው፤ ለችግረኛ ቤተሰቦች በሚሰጠው እርዳታ በ ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ም ሆነ በማገኘው የምግብ ኩፖን (food stamps) እንደ አንድ የቤተሰቤ አባል ተመዝግቧል።ይህንን ሰው እንዴት አድርጌ ነው ከዚህ የማስወጣው ?

የጤና ዋስትና ኢንሹራንስ ያስፈልገኛል በዚህ በ ወረርሽኝ አደጋ ወቅት እንዴት ነው ኢንሹራንስ የማገኘው?

የገብያተኞች ጥበቃ/መከላከያ (Consumer Protection)

ግፍ ፈጻሚዬ በኔ ስም የብድር ካርድ አውጥቷል። ይህንን እሱ የወሰደውን ብድር እምድከፍል ተከስሼአለሁ (ወይም ብድሩን እንድከፈል ውሳኔ ተላልፎብኛል) ። ዕዳ ሰብሳቢዎች ለማበረታቻ ተብሎ ከመንግስት የሚሰጠኝን ክፍያ ሊወስዱ ይችላሉን?

ከመንግስት የሚሰጥ የማበረታቻ ክፍያ

ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች አሉኝ። ሆኖም ኝ ለልጆች የሚሰጥ ተጨማሪ የማበረታቻ ክፍያ( ለምሳሌ በመጋቢት ወር 2020 ላይ ለእያንዳንዱ ልጅ $500፤ በታህሳስ ወር 2020 ደግሞ ለእያንዳንዱ ልጅ $600 ተሰጥቷል፤ እኔ ግን አንዱንም አላገኘሁም። ለምን?

የትኛው ወላጅ ነው ልጆቹ የኔ ናቸው ብሎ የመጠየቅ ህጋዊ መብት ያለው ?

በእኔ ላይ ግፍ የፈጸመው ግለሰብ፤ ለልጅ ማሳደግያ ይከፍለኝ የነበረውን ክፍያ መክፈል ስላቋረጠ ያልተከፈለ የቀድሞ ክፍያ አለበት። ስለዚህ ይሄ ከመንግስት ለማበረታቻ ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ ለእሱ ከሚሰጠው በሙሉ ነው ማግኘት የሚገባኝ ወይስ በከፊል?

ወንጀላዊ

በላዬ ላይ ወንጀል የፈጸመው ግለሰብ በአሁኑ ወቅት በ እስር ላይ ይገኛል። አሁን የኮቪድ አደጋ ባለበት ወቅት ይፈታ ይሆን?


በእኔ ላይ ግፍ የፈጸመው ግለሰብ፤ የተሰጠኝን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ስለጣሰ፤ ክስ ማቅረብ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

ስደተኛነት/ኢሚግሬሽን (Immigration)

ስደተኛ ልጄን በመወከል፤ የወጣት ስደተኞች ልዩ ሁኔታ ማህበር (Special Immigrant Juvenile Status (SIJS) ውስጥ እየተሳተፍኩ ነው። ታድያ ልጄ በቅርቡ አስራ ስምንት ዓመት ስለሚሞላው ከማህበሩ መውጣት አለበት። ይህንን በተመለከተ በዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠን ቀጠሮ አሁንም ይከበርልናል?

## የቤተዘመድ ሁከታ/ብጥብጥ (domestic violence) ምን ማለት ነው?

የቤተዘመድ ሁካታ (Domestic violence) ሲባል **የአስገዳጅነትና የመቆጣጠር** ይዘት ያለው ጠባይ ሲሆን አብዛኛውን ግዜ፤ **አካላዊ ጉዳት የሚያስከትል፡ ስሜታዊ ወይም ስነአእምሮያዊ ጫና የሚያደርግ፤ ወሲባዊ ወይም ገንዘባዊ ማጎሳቆል** የታከለበት ነው (ቁጥጥር ለማድረግ ገንዘብንና ገንዘባዊ ነገሮችን እንደ መሳርያ የሚጠቀም ነው) ።




## አደጋ ሲያጋጥም ከማን ጋር ነው መገናኘት ያለብኝ?

በጣም አስቸኳይ በሆነ አደጋ ውስጥ ካሉ ወደ **9-1-1** ደውሉ ወይም በስልክ ጽሁፍ (text) አድርጉ። [የዲሲ የጥቃት ሰለባዎች መስመር]() ([D.C. Victim Hotline]()) በስልክ፣ በቴክስት ወይም ዌብ ቻት (web chat) 24 ሰዓት ሙሉ ይገኛል። በስልክ ቁጥር **1-844-4HELPDC** (1-844-443-5732) ቢደውሉ ያገኛሉ።

## <u>የሲቪል መከላከያ ትእዛዞች</u>

### የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ምን ማለት ነው?

የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ  በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ፤ የቤተዘመድ ሁካታን በተመለከተ " የእገዳ ትእዛዝ " ወይም '' የመራቅ ትእዛዝ " ብሎ የሚጠራው ነው። በዚህ በቤተዘመድ ሁካታ ያለፈ ሰው፤ ለራሱ ደህንነት ወይም በዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልጆቹን በመወከል፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

### በሲቪል መከላከያ ትእዛዝና በግዚያዊ መከላከያ ትእዛዝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

**ግዚያዊ መከላከያ ትእዛዝ** (Temporary Protection Order) በቤተዘመድ ሁካታ በማለፍ ላይ ያለው ግለሰብ፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲደረግለት ዛሬውኑ ቢጠይቅ፤ ዛሬውኑ ግዚያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ይሰጠዋል፤ ጉዳዩን የፈጸመው ሰው በሌለበትም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይሰማለታል። ይህ ግዜያዊ የሆነ የመከላከያ ትእዛዝ፤ ዳኛው፤ ጥያቄ አቅራቢው *በአስቸኳይ/ድንገተኛ አደጋ ላይ* እንዳለ በመረዳት ለድንገተኛ/አስቸኳይ አደጋ  የሚሰጠው ነው። ይሄው ግዜያዊ የሚባለው ትእዛዝ፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ተጠይቆ ፋይል ከተያዘበትና ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ እስኪሰማ ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ ፤ ልክ እንደ ሲቪል መከለከያ ትእዛዙ ይሰራል። ይሄው ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ለአስራ አራት ቀናት ይቆያል።

**የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ** (Civil Protection Order) ሁለቱ ወገኖች አስፈላጊ ወረቀቶች እንዲሞሉ ከተጠየቁና ፍርድ ቤት የመቅረብ ዕድል ከተሰጣቸውና ከቀረቡ በኋላ የሚሰጥ ነው።ይሄው የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ፤ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከቀረበበት እስከ አንድ ዓመት ድረስ ተግባራዊ ይሆናል።

ግዚያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ለማግኘት ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጎት፤ ወደ ታች በ **<u>Temporary Protection Orders</u>** አርእስት ወደ ተጻፈው ያምሩ።

**ማነው የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችለው?**

ይህንን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ (Civil Protection Order) ለማግኘት የሚጠይቀው ሰው፤ ወሲባዊ ግፍ ወይም በየሄደበት የመታደን ግፍ የተፈጸመበት ካልሆነ በስተቀር፤ ከሚከሰው ሰው *ጋር* **__የግድ__** አንድ ዓይነት **ዝምድና** ያለው መሆን አለበት። ዝምድና መኖር አለበት ሲባል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

- የደም ዝምድና ያላቸው
- የአሁን ወይም የቀድሞ ወዳጆች/ፍቅረኞች ሲሆኑ
- የ*ጋ*ራ ልጅ ያላቸው
- ባለፈው ዓመት ውስጥ የ*ጋ*ራ ቤት የነበራቸው ወይም ጥብቅ ዝምድና የነበራቸው

*ወሲባዊ በደል የደረሰባቸው ን በሰው መሸጥ አደጋ ውስጥ ያለፉ (human trafficking ) ሰዎች፤ ምንም እንኳ ን ከበዳዮቻቸው ጋር __ዝምድና የሌላቸው ቢሆኑም፤__ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ።*

የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጠው የሚጠይቀው ወገን፤ የሚከሰው ሰው በላዩ ላይ አንድ ዓይነት **ወንጀል** እንደፈጸመባቸው ማሳወቅ አለበት። ለምሳሌ ከብዙው በጥቂቱ፤ በደል ከፈጸመ ወይም አካላዊ ጉዳት አድርሳለሁ ብሎ ከዛተ፣ ወሲባዊ በደል ካደረሰ፣ ንብረት ካበላሸ፣ በየቦታው ካሳደደ፣ ሰርቆት ካካሄደ ወይም የልጅ ጠለፋ ካደረገ ወንጀል ፈጸመ ይባላል።

**የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ( Civil Protection Order) የሚያደርገው ምንድነው?**

የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ፤ በቤተሰብ ሁካታ ያለፈው ግለሰብ፤ በላዩ ላይ ወንጀል ከፈጽመው ሰው የሚጠብቁት አስፈላጊና አያሌ መከላከያዎችን ያቀርባል። እነኚህ መከላከያዎች ወይም ጥበቃዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፤

- ግፍ ፈጻሚው፤ ጥቃት እንዳይፈጽም፤ እንዳይዝት፤ በተደጋጋሚ እየተከታተለ እንዳያስፈራራ ይጠይቃል
- ግፍ ፈጻሚው፤ ከተበዳዩ እንዲርቅ ይጠይቃል
- ግፍ ፈጻሚው፤ ከተበዳዩ መኖርያ ቤት፣ የስራ ቦታ፣ መኪና፣ ልጆች፣ ከልጆች ትምህርት ቤት እንዲርቅ
- ግፍ ፈጻሚው፤ ተበዳዩን ወገን በጽሁፍ፣ በስልክ፣በህዝብ መገናኛዎች፣ ወይም በሆነ ዓይነት መንገድ እንዲሁም ሰስተኛ አካል በመጠቀም ለመገናኘት እንዳይሞክር
- የልጅ አሳዳጊነት መብት ለሁለቱ ወገኖች መስጠትና ልጆች ሌላኛውን ወላጅ የሚያዩበት፤ደህንነቱ የተጠበቀ የጉብኝት ቦታ መመደብ
- በቤት ውስጥ በተፈጠረ ሁከት ምክንያት የተከተለ ወጪ ካለ ወንጄል ፈጻሚው ወገን ለሌላኛው መልሶ መስጠት
- ወንጄል ፈጻሚው ወገን፡ በፍርድ ቤቱ አገልግሎቶችና በበደለኛ ክትትል ተቋም (Court Services and Offender Supervision Agency (CSOSA) የሚሰጡትን ትምህርቶች እንዲከታተል ማድረግ

## በኮቪድ-19 (COVID-19) አደገኛ ወቅት እንዴት ነው የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲደረግልኝ መጠየቅ የምችለው?

ምንም እንኳን በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት፤  የዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና ሁለቱ የቤተዘመድ ሁከት ማእከሎች ለህዝብ የተዘጉ ቢሆኑም፤ የሲቪል መከለከያ ትእዛዝ እንዲሰጦት አሁንም መጠየቅ ይችላሉ።

ይህንን  የሲቪል መከለከያ ትእዛዝ Petition for a Civil Protection Order እንዲሰጦት ማመልከት ከፈለጉ ወደ www.probono.net/dccourts መግባት ያስፈልጎታል። ፎርሙን ይሙሉትና በዌብሳያቱ መላክ ይችላሉ ወይም  ፎርሞቹን ያውጡና  ወደ DVD@dcsc.gov  በኢሜል ይላኩ። ጥያቄ ወይም የሆነ የሚያሳስብ ነገር ካሎት በስልክ ቁጥር (**202) 879-0157**  ከጸሃፊው መስርያ ቤት (Clerk's Office) ጋር ተገናኙ ወይም ወደ DVD@dcsc.gov  ኢሜል ያድርጉ።

**ዲሲ ሴፍ** (D.C. SAFE) የተባለው ተቋም፤ በቤተዘመድ ሁከት ያለፉ ግለሰቦች፤ ይህንን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝን ለመጠየቅ፤ ፎርም እንዴት እንደሚሞላና እንደሚላክ በተመለከተ እርዳታውን ይለግሳል። በተጨማሪም ዲሲ ሴፍ (D.C. SAFE) ፡ በደል የተፈጸመባቸውን ግለሰቦች እንዴ ማህበራዊ አገልግሎቶችን፣ ይህግ አገልግሎቶችንና መሰረታዊ የኑሮ አስፈላጊዎችን በማቅረብ ይተጋገዛል። እንደ ደንቡ ከሆነ ከዲሲ ሴፍ (D.C. SAFE) ጠበቃ ጋር ከሁለቱ የቤተዘመድ ሁካታ ማእከሎች በአንዱ በአካል ተገናኝተው ይነጋገራሉ። በአሁኑ ግዜ ግን በኮቪድ የወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ማእከሎቹ ለግዜው ተዘግተዋል

የዲሲ ሴፍ (D.C. SAFE) ጠበቃዎች ከሩቅ ሆነው በስልክ ወይም በኦንላይን ነው እርዳታቸውን ግፍ ለተፈጸመባቸው ግለሰቦች የሚሰጡት። የግፍ ሰለባዎች ጉዳያቸውን በሚመለከት አቤቱታ እንዴት እንደሚጻፍና ለፍርድ ቤት እንዴት እንደሚቀርብ በማስመልከት እርዳታቸውን ይሰጧቸዋል። ከዲሲ ሴፍ (D.C. SAFE) ጋር ለመገናኘት ወደ ዲሲ የግፍ ሰለባዎች መስመር D.C. Victim Hotline በስልክ ቁጥር **1-844-4HELPDC** (1-844-443-5732) በመደወል ወይም በጹሁፍ ቴክስት በማድረግ ተገናኙ።

## ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዞች

### እንዴት ነው ይህንን ግዜያዊ የመከለከያ ትእዛዝ ማግኘት የምችለው?

የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ በፍርድ ቤቱ እንዲሰጦት አቤቱታዎን ካቀረቡ፤ የግዜያዊ የመከለከያ ት እዛዝም ማግኘት ካለቦት፤ በፎርሙ ወይም በአቤቱታው ወረቀት፤ ሁለተኛው ገጽ ላይ ተመላክቶ በሚገኘው ሳጥን፤ ልክ ከወደታች እንደሚታየው የኤክስ ምልክት ያስቀምጡ።

16. ☒ የመልስ ሰጪው እርምጃዎች የእኔንና የቤተሰቤን ደህንነት ወድያውኑ አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ ፍርድቤቱ ዛሬውኑ ግዜያዊ የጥበቃ ትእዛዝ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ።

የዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የቤተዘመድ ሁከት መስርያ ቤቶች ከሩቅ በኦንላይን ብቻ ስለሚሰሩ፤ እርስዎም ጉዳዮን የሚመለከት አቤቱታዎን በመሙላት በዚህ በሚከተለው

አድራሻ ኦንላይን http://www.probono.net/dccourts በመግባት ያስገቡ።ወይም ፎርሙን ያውጡና ወደ DVD@dcsc.gov ኢሜል ያድርጉ። ጥያቄ ወይም የሚያሳስበት ነገር ካለ የጸሃፊውን መስርያ ቤት (Clerk's Office) በስልክ ቁጥር **(202) 879-0157** በመደወል ወይም ወደ DVD@dcsc.gov በመግባት ኢሜል ያድርጉ።

## ከስራ ሰዓታት ውጪ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ቢያስፈልገኝስ?

ከስራ ሰዓታት ውጪ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ ቢያስፈልጎ፤ ለአደጋ ግዜ በአስቸኳይ የሚሰጥ ግዜያዊ

ትእዛዝ (Emergency Temporary Protection Order, ኢ-ቲ-ፒ-ኦ ETPO) እንዲሰጦት መጠየቅ ይችላሉ። ይህ የ ኢ-ቲ-ፒ-ኦ አስቸኳይ ትእዛዝ ጽህፈት ቤት 24 ሰዓት ክፍት ነው።

ይህንን የ ኢ-ቲ-ፒ-ኦ (ETPO) ሂደት ለመተግበር (1) ወደ 9-1-1 መደወል ወይም የጽሁፍ መለክት መላክ (ቴክስት ማድረግ (2) ወደ **ዲሲ ሰለባዎች አስቸኳይ መስመር** (D.C. Victim Hotline) በስልክ ቁጥር **1-844-4HELPDC** (1-844-443-5732) ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ ወይም (3) ወደ ሰባተኛው የዲስትሪክት ፖሊስ ጣብያ (Seventh District Police Station) በአካል በመሄድ ብቁ መሆንዎን ያረጋገጡ።

## የተሰጠኝ ግዜያዊ የመከለከያ ትእዛዝ እስከ ስንት ግዜ ይቆያል?

እንደ ደንቡ ከሆነ፤ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዛት (Temporary Protection Orders) ለ14 ቀናት ነው የሚሰጡት። ይሁንና በዚህ በገባው የ ኮቪድ (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የቤተዘመድ ሁካታ ክፍል፤ ሁሉም አዲሶች የግዜያዊ መከላከያ ትእዛዞች እስከ ሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ድረስ እንዲቆዩ አዟል።

## መርሃ ግብር (Scheduling) ማውጣትና ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች

## የሲቪል መከላከያ ትእዛዜን ለመቀበል መቼ ነው ፍርድ ቤት የምሄደው?

ጉዳይዎን ፋይል ሲያደርጉ የችሎት ማሳወቂያ እና የመጥሪያ ትዕዛዝ መቀበል አለብዎት። ይህ ማሳወቂያ በፍርድ ቤት ቀነ ቀጠሮዎ ላይ የቨርቹዋል ችሎቱን እንዴት እንደሚቀላቀሉ

የሚያሰዩ መረጃዎችን እና ትዕዛዛትን ያካትታል። የፍርድ ቤት ቀነ ቀጠሮዎ በቨርቹዋል የሚቀጥልበት ዕድል አለ። ምንም ነገር ካልሰሙ ኢሜይልዎን ይመልከቱ ወይም ከፍርድ ቤት ቀነ ቀጠሮው በፊት ፍርድ ቤቱን ያነጋግሩ።

ቀነ ቀጠሮውን በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት፣ የቤተዘመድ ሁካታ ጽህፈት ቤት የጸሃፊ መስርያ ቤትን በስልክ ቁጥር (**202) 879-0157** በመደወል ወይም በኢሜል ወደ DVD @ dcsc.gov በመጻፍ ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ ከጥዋቱ 8:30 እስከ 5:00 ከሰዓት በኋላ ባለው ግዜ ውስጥ ተነጋገሩ።

## ጉዳዬ በሚሰማበት ወቅት፤ ችሎቱ በቨርቿል ከሆነ ምንድነው የሚሆነው?

ጉዳዮ በቨርችዋል (WebEx) መንገድ በቪድዮ የሚሰማ ከሆነ፤ ስልክ ደውለው በችሎቱ ለመካፈል ይጠይቁ ከዛም ከጥዋቱ 8:30 ተቀላቀሉ። እነኚህ መመርያዎች ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ የሚሰጡት ናቸው።
(የቨርቹዋል ፍርድቤቱን ለመስማት የተሰጠ መመርያ (Instructions to Join the Virtual Hearing)

ፍርድ ቤቱ ሁሉም ወገኖች በቪድዮ የሚካሄደውን ችሎት በዌቤክስ (WEBEX) ይህም የካሜራ አቅርቦት ካሎት
እንዲከታተሉ ይጠይቃል። ከተቻሎት ይህንንበ የዌቤክስ (WEBEX) አፕ ወደ ስልኮ፣ ታብሌቶ ወይም ኮምፑተሮ
ይህንን ማያያዣ(ሊንክ) https// www.webex.com/downloads.html በመጠቀም አሽጋግሩ።
ወደሚካሄደው ችሎት ለመግባት ይህንን ሊንክ https://dccourts.webex.com/meet/dvdhearing ይጫኑ።
በችሎቱ ውስጥ ለመግባትና በቪድዮ ለመስማት ጉጉል ክሮምን ተጠቀሙ። ይህንና ኢንተርኔት አክስፐሎረርን
(Internet Explorer), ሳፋሪና (safari) የመሳሰሉትንና ሌሎችንም መጠቀም ይችላሉ።
ማያያዣው ወይም ሊንኩ ካልሰራ፤ እዚህ https://dcourts.webex.com ውስጥ በመግባትና ሚስጢራዊ ኮድ
ወይም ቁጥር 173 720 1234 በመጻፍ ሊገቡ ይችላሉ።
ቴክኒካዊ ጥያቄ ካሎት ወደ ፍርድ ቤቱ የመሙላትና የቴክኖሎጂ ቅርንጫፍ ክፍል (Courtroom Recording
and Technology Branch) በስልክ ቁጥር 202-879-1928 የውስጥ መስመር 2 ይደውሉ።
ፍርድ ቤቱ በቪድዮ ግንኙነት ቢያደርጉ ይመርጣል። በዚህ ለመገናኘት አስቸጋሪ ከሆኖበት ግን ወደ ዳኛው

ጽህፈት ቤት ደውለው ቀጠሮዎ መቼ እንደሆነ ይጠይቁ። የዳኛ ሊ (Judge Lee) ጽህፈት ቤት(የፍርድ ቤት ክፍል 113) በስልክ ቁጥር 202-879-0200፣ የዳኛ ኖዌልስ( Judge Knowles) ጽህፈት ቤት ( የፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 114) ደግሞ በስልክ ቁጥር 202-879- 8750 በመደወል ሊገናኙ ይችላ።የሆነ ሰው ስልኩን ካነሳ ስለ ችሎቱ ሰዓት መረጃ ሊሰጦት ይችላል። ስልኩን ማንም ሰው ካላነሳው ግን መለክቶን ይተውና በተፋጠነ መልክ አንድ ሰው ይደወልሎትንና መረጃ ይሰጦታል። በተሰጠው ግዜ መገኘት አለቦት።

የቨርቹዋል ችሎቱን ለመቀላቀል የሚረዱ መመሪያዎች

ፍርድ ቤቱ ሁሉም ወገኖች የርቀት ችሎቱን በ WebEx መተግበሪያ (ካሜራ የሚያገኙ ከሆነ) በቪዲዮ እንዲቀላቀሉ ይጠይቃል። የሚችሉ ከሆነ፣ የሚከተለውን ሊንክ፦ https://www.webex.com/downloads.html በመጫን የ WebEx መተግበሪያውን በስልክዎ፣ በታብሌትዎ ወይም በኮምፒውተርዎ ማውረድ አለብዎት።

ችሎቱን በቪዲዮ ለመቀላቀል፣ እባክዎ ይህን ሊንክ https://dccourts.webex.com/meet/dvdhearings ይጫኑ።

ችሎቱን በቪዲዮ የሚቀላቀሉበት ሊንክ በ Google Chrome የድር አሳሽን በመጠቀም በደንብ ይሰራል፣ ሆኖም Internet Explorer፣ Safari፣ ወይም ሌላ ማንኛውም የኢንተርኔት አሳሽን መጠቀም መቻል አለብዎት። ሊንኩ የማይሰራ ከሆነ፣ https://dccourts.webex.com ን በመጎብኘት እና 173 720 1234 የሆነውን የስብሰባውን ኮድ በመጻፍ መቀላቀል ይችላሉ።

ችሎቱን ስለመቀላቀል ላሉ ቴክኒካል ጥያቄዎች፣ የፍርድ ቤት የመረጃ ክፍል እና የቴክኖሎጂ ቅርንጫፍን በ 202-879-1928፣ አማራጭ 2 ላይ ያነጋግሩ።

በ ዌባኤክስ (WebEx ) በኩል ለማረጋገጥ ሲደውሉ አንድ ጽሃፊ መረጃዎን እንዲሰጡ ይጠይቃል። ነገሩን የሚያስማም ሰው ሲገኝ ፤ ፍርድ ቤት ራሱ በመደወል ዳኛው ጉዳዮን ለመስማት ዝግጁ ሲሆን ይደውልሎታል። ከስልኩ አጠገብ መሆንን አይዘንጉ፤ በዛው ቀን ከከሰዓት በኋላ፤ ከ5:00 ሰዓት በፊት ከፍርድ ቤት እንደሚደወልሎት ይወቁ።

## በወቅቱ ያለኝን ግዚያዊ ወይም የሲቪል መከላከያ ትእዛዞችን ማራዝም ብፈልግ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?

**ጉዳይን ለማሻሻል ወይም ለማራዘም የሚደረግ ጥያቄ** (Motion to Modify or Extend) የተሰኘ ውስጥ በመግባት የሲቪልም ሆነ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዞች፤ ቀናቸው ከማለፉ በፊት፤ ፎርም በመሙላት ማራዘም ይቻላል።ካለበለዝያ በአዲስ ሁኔታዎች የተመረኮዘ አዲስ አቤቱታ መሙላት ሊያስፈልግ ነው ማለት ነው።

የቤተዘመድ ሁከታ ክፍል የጸሃፊው መስርያ ቤት፤ በኦንላይን የተደረጉ ማመልከቻዎችንና አቤቱታዎችን በመቀበል ላይ ነው። በኦንላይን ወደ www.probono.net/dccourts በመግባት የጀመሩትን አቤቱታ አጠናቅቁና አስገቡ።ወይም በኢሜል አድራሻ ወደ DVD@dcsc.gov በመግባት ማመልከቻዎን ያጠናቅቁ።

የትኛውን ፎርም መጠቀም እንዳለበት ማወቅ ካዳገቶት ወይም የሚፈልጉት ፎርም ከሌለ፤ በስልክ ቁጥር (**202) 879-0157** በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻ DVD@dcsc.gov በመጻፍ ከጸሃፊው ጽህፈት ቤት ጋር ተገናኙ።

## የህግ እርዳታ

በዚህ በኮቪድ-19 ወቅት፤ ምንም እንኳን እንደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) የመሳሰሉ ቦታዎች የተዘጉ ቢሆኑም፤ አሁንም እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

የሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጠበቃዎች፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ለማግኘት የሚፈልጉ ግለሰቦችን ምክርና እርዳታ ለመስጠት ተዘጋጅተዋል። በኖርትዌስትና በሳውዝኢስት (Northwest and Southeast) የሚገኙ ጽህፈት ቤቶቻችን ለህዝብ ዝግ ናቸው ይሁንና

በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161**በመደወል ወይም online በመግባት አገልግሎታችንን የሚሹ ከሆነ ማማልከት ይችላሉ።

ክፍት የሆኑና እርዳታ የሚሰጡ አያሌ ሌሎች የህግ አገልግሎት ሰጪዎችም አሉ።

## ምክርና ድጋፍ (Counseling and Support)

### ለምክርና ለድጋፍ ወይም የደህንነት ዕቅድ ለማውጣት ከማን ጋር ልገናኝ?

የሚከተሉት ድርጅቶች ምክርና/ወይም ደህንነትን በሚመለከት ዕቅድ የማውጣት እገዛ የሚያደርጉ ናቸው

- የዌንድት ማእከል (The Wendt Center) በቤተዘመድ ሁከት ያለፉ ፤ ወሲባዊ ግፍ የተፈጸመባቸው፤ ከሌላ አገር በግዴታ መጥተው የተሸጡ፤ የግድያ ሙከራ የደረሰባቸው ና ሌሎች አስፈሪ ወንጀሎች የተፈጸመባቸውንሰዎች የሚመክር ድርጀት ነው። እነሱም በስልክ ቁጥር 202) 204-5021 ይገኛሉ።
- የሴቶች ማእከል (Women's Center) በቤተሰብ ሁከት ላለፉ ሴቶች ምክር ይሰጣል። እነሱም በስልክ ቁጥር (202) 293-4580 በውስጥ መስመር 100 በመደወል ከባለሙያ ጋር እንዲነጋገሩ ይረዳሉ
- የኤስያዊ ፓሲፊክ ደሴተኞች የቤተዘመድ ሁከት የምንጭ ፕሮጄክት -ዲ-ቪ-አር-ፒ (Asian/Pacific Islander Domestic Violence Resource Project, DVRP) በስልክ ቁጥር (202) 833-2233 የአስቸኳይ ጉዳይ መስመር ቢደውሉ ከጉዳይ አስተዳዳሪዎች ጋር ሊገናኙ ይችላሉ።
- **ጄ-ሲ-ኤ-ዲ-ኤ** (JCADA) ሚስጢር የሚጠብቅ ከሰኞ እስከ ሃሙስ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ 5:00 ከሰዓት በኋላ፤ ዘወትር ዓርብ ደግሞ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ 3:00 ሰዓት ድረስ  በስልክ ቁጥር 1-877-88-JCADA ቢደውሉ፤ መረጃ፣ ድጋፍና የደህንነት ዕቅዶችን ለማውጣት እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ።
- **ዶን** (DAWN) የመስማት ችግር ያላቸውና በዚህ በቤተሰብ ሁከት ያለፉ ግለሰቦችን ያግዛል። ከእነሱም ጋር ለመገናኘት፤ በዚህ ኢሜል hotline@deafdawn.org. ሊያገኙዋቸው ይችላሉ።

- **ዲሲ ሴፍ** (D.C. SAFE) ደግሞ የደህንነት እቅድ ለማውጣት ይተባበራል። ወደ ዲሲ የሰለባዎች አስቸኳይ መስመርም (D.C. Victim Hotline) በስልክ ቁጥር 1-844-4HELPDC (1-844-443-5732) ሊገኙ ይችላሉ።

## የልጅ አሳዳጊነት መብት (Custody)

### የልጅ አሳዳጊ መብት እንዲሰጠኝ እንዴት ነው ጥያቄ ማቅረብ የምችለው፤ ባለኝ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ ላቀርብ እችላለሁን?

ወደ https://www.probono.net/dccourts/familycourt/ ይግቡና ተገቢውን ፎርም ይሙሉ። አንዴ ፎርሙን ሞልተው ካገባደዱ በኋላ ሁለት ዓይነት መንገዶች አሉ ማስገባት የሚያስችሉት፤

- የሚከፈል ዋጋን የሚያነሳ ፍቃድ ካሎት ወይም ምንም እንዳይከፍሉ መጠየቅ ከፈለጉ፤ ፎርሙን ወደ familycourtcic@dcsc.gov ኢሜል አድርጉ።
- የሚከፈል ዋጋን የሚያነሳ ፍቃድ ካሎት፣ ወይም የሚከፈል ዋጋ ለማንሳት ፈቃድ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ሰነዶችዎን ማተም እና በ ዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 500 Indiana Avenue, NW ላይ በሚገኘው ዋና መግቢያ በር ላይ ያከው የውስጥ ጉዳዮች ግንኙነቶች ሳጥን ላይ ሊያስገቡት ይችላሉ።
- ገንዘብ እንዳትከፍሉ የሚያደርግ ፈቃድ ከሌሎት ወይም እሱን ለማግኘት ብቁ ካልሆኑ፤ በ Case File Xpress አካውንት መጀመር ይችላሉ ከዛ በውሃላ በኤሌክትሮኒክስ ፎርሞን መሙላትና መላክ ይችላሉ።

ጉዳዮን በማርቀቅም ሆነ ከረቀቀ በኋላ በማስገባት ላይ እርዳታ ከፈለጉ **የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስን በራስ መቻል የተሰኘውን ማእከል** (Family Court Self-Help Center) ጋር በስልክ ቁጥር **(202) 879-0096** ተገናኙ።

**በግዚያዊ የመከላከያ ትእዛዝ በኩል ያገኘሁት የልጅ ማሳደግ መብት አለኝ። ይህ ትእዛዝ እንዲቆይልኝ ወይም እንዲራዘምልኝ አዲስ የልጅ ማሳደግያ ፋይል መክፈት አለብኝን ?**

ምናልባት፣ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ለማግኘት ሲሄዱ ያኔ የሲቪል መከላከያ ትእዛዙ እስካለ ድረስና እሱ እስከጸናበት ግዜ ድረስ የልጅ ማሳደግያ መብቶ የጸና ይሆናል። ይሄ ግዜያዊ የመከለከያ ትእዛዝ እስኪገባደድ ድረስ፤ የልጅ አሳዳጊነት መብት ካልተሰጦት፤ ያኔ አዲስ የልጅ ማሳደግ መብት እንዲሰጦት ያመለክታሉ።

የልጅ አሳዳጊ መብት እንዲሰጦት ማመልከትን ግምት ውስጥ ለማስገባት ከፈልጉ፤ ጥያቄ ለማቅረብና ላለማቅረብ መወሰን ላይ እንዲያግዞት ጠበቃ ማነጋገር ጥሩ ነው። የሊጋል ኤድ (Legal Aid) ፤ የሳውትዌስትና ሳውትኢስት (Northwest እና Southeast) ጽህፈት ቤቶቻችን ለህዝብ የተዘጉ ቢሆኑም፤ አገልግሎታችንን ለማግኘት በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161** በመደወል ወይም በ online በመግባት ማመልከት ይችላሉ።

**ሌላኛው ወላጅ በልጃችን ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ ነው የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ልጃችን፤ ያኛውን ወላጅ ለብቻው ሂዶ ሲያይ ደህንነቱ ይጠበቃል የሚል ስሜት የለኝም። ምን ማድረግ አለብኝ ?**

ይህ በነገሮች ላይ የሚሞረኮዝ ነው። የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ከሌሎት፤ ልጅዎን በመወከል፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ለማግኘት ማመልከቻ አስገብተው፤ ልጅ የማሳደግ መብት የሚሰጦትና ግፍ ፈጻሚው ከልጅዎ ጋር የሚያደረገውን ጉብኝት እንዲታገድ የሚያደርግ ግዜያዊ የመከላከል ትእዛዝ ሊያገኙ ይችላሉ። ይችላሉ። ከወደላይ ሰፍሮ የሚገኘውን እንዴት የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ጥያቄ እንዴት እንደሚያቀርቡ የሚጠቁም (how to file for a Civil Protection Order) ተመልከቱ።

ለግፍ ፈጻሚው የጉብኝት ዕድል የሚሰጥ፤ የልጅ አሳዳጊ መብት የሚሰጦት ትእዛዝ ካሎት አስቸኳይ የልጅ አሳዳጊ መብትን የሚያሻሽል ጥያቄ **Emergency** Motion to Modify

Custody ለፍርድ ቤት አስገቡ። እዚህ ላይ **የአስቸኳይ ግዜ** ፎርም በመሙላት ላይ መሆንዎን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በስልክ ቁጥር **(202) 442-6100 ወደ** ልጅና ቤተሰብ አገልግሎት ተቋም (Child and Family Services Agency (CFSA) ደውለው ያስታውቁ ወይም **24 ሰዓታት** ለማይዘጋው የአስቸኳይ ግዜ መስመራቸው ጋ በስልክ ቁጥር **(202) 671-7233** ደውለው በልጅዎ ላይ ስለሚፈጸመው ግፍ ሪፖርት ያድርጉ።

**በእኔ ላይ ግፍ የሚፈጽመው ሰው ግፍ ፈጽሞብኛል፤ ወይም እያስፈራራኝ ነው። በአሁኑ ወቅት ልጃችንን እንዲጎበኝ ማድረግ ከልጃችን ደህንነት አንጻርጋር አመዛዝኜ ሳየው ትክክል አይደለም የሚል ስሜት አለኝ። ምን ማድረግ አለብኝ?**

ይህም በሌሎች ነገሮች ላይ የተመረኮዘ ነው። የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ከሌሎት፤ ልጅዎን በመወከል፤ **የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ** ( Civil Protection Order )ለማግኘት ማመልከቻ አስገብተው፤ ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጦት ጠይቁ። ለራሰ ደህንነት መከላከያ ከመጠየቆ በተጨማሪ ይሄው የጠየቁት ግዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ፤ የግፍ ፈጻሚውን የልጅ መጎብኘት መብት የሚከለክል እንዲሆን ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ሌላ መገናኛ ቦታ እንዲመቻች መጠየቅ ይችላሉ።

ለግፍ ፈጻሚው የጉብኝት ዕድል የሚሰጥ፤ የልጅ አሳዳጊ መብት የሚሰጦት ትእዛዝ ካሎት አስቸኳይ የልጅ አሳዳጊ መብትን የሚያሻሽል ጥያቄ (Emergency Motion to Modify Custody) ለፍርድ ቤት አስገቡ። እዚህ ላይ **የአስቸኳይ ግዜ** ፎርም በመሙላት ላይ መሆንዎን በትክክል ማረጋገጥ ያስፈልጋል።ለራስዎ ደህንነት ሲሉም የሲቪል ደህነንት ፎርም ይሙሉ። ግን የቤተዘመድ ሁካታ ዳኞች፤ በወቅቱ የሚሰራበትን የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዞችን ለመቀየር አብዛኛውን ግዜ ዝግጁ አይደሉም። በመሆኑም ዳኛው፤ ያቀረቡትን የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝን ማሻሻል የሚለው ጥያቄዎን ላይቀበለው ይችላል።ወይም ለአጭር ግዜ ብቻ እንዲሻሻል ሊወሰን ይችላል። በተጨማሪም፤ ግዜያዊ የመከላከል ትእዛዙ የሚደረገውን ጉብኝት በግዜያዊነት እንዲቆም ቢያደርግ፤ ዋናውን የልጅ አሳዳጊነት ጥያቂ የመሻሻል ፎርምን Motion to Modify Custody እንዲሞሉ ሊጠየቁ ይችላሉ።

**ያለኝ ወቅታዊ የሲቪል መከለከያ ትእዛዝና የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ሁለቱም በልጅና በወላጅ መካከል ለሚደረጉ ጉብኝቶች መቀባበሉ ታዛቢ ባለበት የጉብኝት ማእከል እንዲሆን ነው የሚያዙት ስለዚህ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ታዛቢ ያለበት ጉብኝት ማዕከል፤ ታዛቢዎች፤ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ በሩቅ ሆነው እንዲታዘቡ ለማድረግ  እየሰራ ነው። ለተጨማሪ መረጃ ለማግኘትም የታዛቢ ያለበት ጉብኝት ማዕከሉን በስልክ ቁጥር (202) 879-4253 በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

በእርስዎ ዘንድ ታዛቢ ከሩቅ ሆኖ የሚታዝብበት ሁኔታ ገና ካልተዘጋጀልዎት፣ እርስዎ በአሁኑ ግዜ፤ ሁኔታው እንዲረዳዎትና በተቻለ መጠን ትክክለኛውን አማራጭ እንዲወስዱ ይጠበቅቦታል። ታዛቢ ያለበትን የጉብኝት ቦታ ለመተካት ሌሎች አማራጮች እንዳሉ ያጥኑ። አመቺ ከሆነ፤ ስለዚሁም ከሌላኛው ወገን ጋር ለመረዳዳት ሞክሩ።

እርሶና ሌላኛው ወገን፤ ከተፈቀደው ታዛቢ ካለበት የጉብኝት ቦታ ውጪ፤ በሌላ ቦታ አመቺነት ስምምነት ላይ ካልደረሳችሁ፤ ባሎት ሲቪል መከለከያ ትእዛዞ ወይም የአሳዳጊነት መብት ትእዛዞ ላይ ለውጥ ወይም መሻሻል እንዲደርግሎ ለፍርድ ቤቱ ማመልከት ይቻላሉ።ዳኛው፤ ታዛቢ ያለበት የጉብኝት ማእከሉ እስኪከፈት ድረስ ጉብኝቱ እንዲቋረጥ ሊያዝ ይችላል።  ግን ማስታወስ ያለበት፤ አብዛኛውን ግዜ ዳኞች፤ እርሶ ከሌላኛው ወገን ጋር ምቹ የሆነ የመገናኝያ ቦታ ለማግኘት በቅንነት የጣሩ መሆኑን ሲያውቁ፡ ላቀረቡት ጥያቄ ጥሩ ግምት ሊሰጡ የሚችሉት።

ያሎትን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ለማሻሻል ከወሰኑ፤ ልክ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ለማግኘት የሞሉት ዓይነት ፎርም filing for a Civil Protection Order ነው አሁንም የሚሞሉት።

የልጅ አሳዳጊነት መብትን ለማሻሻል ጥያቄ ማቅረብ ከፈለጉ፤ procedure for filing a motion in your existing custody case የሚለውን ተከተሉ።

**ያለኝ የሲቪል መከላከያ ትእዛዝና የአሳዳጊ መብት ትእዛዝ የሚጠይቁት በአንዱ ወገንና በሌላው ወገን የሚደርግ የልጆች ቅብብሎሽ  ታዛቢ ባለበት በጉብኝት ማእከሉ ብቻ እንዲሆን የሚያዝ ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?**

በዚህን ወቅት፤ የወላጅና የልጅ ጉብኝት ቀጣይነት እንዲኖረው፤ ልጅ በምተለዋወጡበት ግዜ፤ የመለዋውጫ ቦታው ደህነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።የእርሶ ደህንነትም እንዲጠበቅ፤  የልጅ ልውውጦች በፖሊስ ጣብያዎች፣ ሶስተኛ አካል ባለበትና በመሳሰሉት መሆናቸውን አረጋግጡ። በዚህን ወቅት፤ ጉዳዮችን ለመረዳት ክፍት አእምሮ አሳድሩ። ዳኞች፤ በተቻለ መጠን የተደረሰውን የጉብኝት ሁኔታን እንደትረዱና እንድትቀበሉ ይፈልጋሉ።

እርሶና ሌላኛው ወገን፤ ልጆችዎን ለመቀባበል፤ ታዛቢ ካለው የጉብኝት ማእከል ውጪ፤ ደህነንቱ የተጠበቀ ተገቢ ቦታ ማግኘት ካልቻላችሁ፤ የሲቪል መከላከያ ትእዛዞን ወይም የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዞን ለማስተካከል ወይም ለማሻሻል የሚያስችሎትን ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ ማስገባትን ግምት ውስጥ አስገቡ።ዳኞች፤ የሌላውን ወገን ልጆችን የመጠየቅ መብትን ሊገፉ አይችሉም ግን ሌሎች አዳዲስ አማራጮችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ልጆች ወላጅን፤ ወላጅ ደግሞ ልጆቹን ለማየት እንዲችል ከልብ የመጎብኝያ ቦታ ለማግኘት ከሞከሩ ዳኞች ለጥያቄዎ አዎንታዊ መልስ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

የሲቪል መከላከያ ትእዛዞን ለማሻሻል ከፈለጉ፤ ት እዛዙን ለማገኘት የተጠቀሙበትን መንገድ (filing for a Civil Protection Order) ይከተሉ።

ያለውን የአሳዳጊነት መብትን ለማሻሻል ከፈለጉ፤ ያሎትን የአሳዳግነት መብት ትእዛዝን procedure for filing a motion in your existing custody caseተከታተሉ።

## ፍቺ (Divorce)

### ባለቤቴ ገንዘባችንን የሚቆጣጠር እርሱ ነው። እና እጄን በገንዘብ ጉዳይ ውስጥ እንዳልከት ከልክሎኛል። ያሉኝ አማራጮች ምንድናቸው ?

ተጋብታችሁ ከሆነና ገንዘባዊ በደል እያደረሰቦ ከሆነ፤ ለቤተሰብ ፍርድ ቤት ወይም ለቤተዘመድ ሁከት ክፍል አቤቱታዎን በማቅረብ መፍትሄ ለማግኘት ይችላሉ። ምን ዓይነት አቤቱታ እንደሚያቀርቡና ምን ዓይነት መፍትሄ እንደሚያገኙ የሚወስነው ሁኔታዎን ለማስረዳት የሚያቀርቡት ዝርዝር ገለጻ ነው። ሊጋል ኤድ (Legal Aid) ያሎትን ምርጫዎች የትኛዎቹን ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለቦት ሊረዳዎት ይችላል።
በኖርትዌስትና በሳውዝኢስት (Northwest and Southeast) የሚገኙ ጽህፈት ቤቶቻችን ለህዝብ ዝግ ናቸው ይሁንና በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161**በመደወል ወይም online በመግባት አገልግሎታችንን የሚሹ ከሆነ ማማልከት ይችላሉ።

## መኖርያ ቤት (Housing)

### ጉዳት የሚያደርስብኝን ሰው ጥዬ መውጣት አለብኝ። የቤተዘመድ ግፍ የደረሰባቸው ሰዎች የሚቆዩባቸው መጠግያ ቦታዎች አሁንም በዚህ በወረርሽኝ አደጋ ግዜ ክፍት ናቸውን ?

አዎን። በ **ዲሲ ሴፍ** (D.C. SAFE) ፤ **ማይ ሲስተርስ ፕሌስ** (My Sister's Place) ፤ **በዳሽ** (DASH - የዲሲ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኖርያ ቦታ ትብብር - District Alliance for Safe Housing) የሚካሄዱ የቤተዘመድ ግፍ የደረሰባቸው ሰዎች የሚቆዩባቸው መጠግያ ቦታዎች አሉ። እንዲሁም **ሃውስ ኦፍ ሩት** (House of Ruth) አሁንም ክፍት ነው። ቦታዎቹን በንጽህና ለመያዝም አዲስ አገባቦችን እየተከተሉ ናቸው። መኖርያ ቤት የሚፈልጉ፤ በቤተዘምድ ግፍ በማለፍ ላይ ያሉ ሰዎች፤ በስልክ ቁጥር **1-844-4HELPDC (1-844-443-5732)** ወደ **ዲሲ ሰለባዎች አስቸኳይ መስመር** (D.C. Victim Hotline) መደወል ወይም የስልክ መለክት ማድረግ ይችላሉ።

ተጨማሪ የመኖርያ ቦታዎች መረጃም እንደሚከተለው ነው፤

- **ዳሽ** DASH ዘወትር ሮብ ከሰዓቱ 1:30 እስከ 3:30 የስልክ ምክር ይሰጣል ይህም በስልክ ቁጥር (**202) 290-2356 x 101** በመደወል ይገኛል
- መጠግያ ቦታ የሚያስፈልገው ማንኛውም ሰው ወደ **ዲሲ መጠግያ አስቸኳይ መስመር (**D.C. Shelter Hotline) **በስልክ ቁጥር** (**202) 399-7093** መደውል ይችላል።

### ከ የወንጀል ሰለባዎች እርዳታ ፕሮግራም (Crime Victims Compensation Program) እርዳታ ማግኘት እችላለሁን?

ከ ሚያዝያ 5 ቀን 2021 ጀምሮ፡ የወንጀል ሰለባዎች እርዳታ ፕሮግራም (Crime Victims Compensation Program) ፤ በአካል ዘወትር ሰኞ፣ ሮብና ዓርብ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 4:00 ሰዓት በ 500 ኢንዲያና አቬኑ ኖርትዌስት ዋሺንግተን ዲሲ 20001 (500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001) ይገኛል። ሰራተኞች በመጀመርያው ደረጃ  መረጃ መስጫ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።

የቤተዘመድ ግፍ የደረሰባቸው ግለሰቦች፤ **ሲ-ቪ-ሲ-ፒ** (CVCP) ን በቀጥታ በስልክ ቁጥር (**202) 879-4216** በመደወል ወይም ወደ **ዲሲ የሰለባዎች አስቸኳይ መስመር** (D.C. Victim Hotline) በስልክ ቁጥር **1-844-4HELPDC (1-844-443-5732)** በመደወል እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

### በቤት ውላችን ውስጥ ግፍ ፈጻሚዬና እኔ ተዘርዝረናል። ከግፍ ፈጻሚዬ ጋር አንድ ቤት መኖር  ሰላም አይሰማኝም።  በዚህ ባለንበት የወረርሽን ወቅት ከቤት እንዲወጣልኝ ላስገድደው እችላለሁን?

ይቻል ይሆናል። የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ እንዲሰጥሽ ፍርድ ቤት ካመለክትሽ፤ በዛውም የቤተዘመድ ግፍ የሚፈጽምብሽ ግለሰብ ከጋራ ቤታችሁ እንዲወጣልሽ መጠየቅ ትችያለሽ።ከፍ ያለ አደጋ ላይ እገኛለሁ ካልሽ፡ ወድያውኑ ግዜያዊ የመከላከል ትእዛዝ ይሰጠኝ ብለሽ መጠየቅ ትችያለሽ፡ ወድያውኑ፤ በዛው ቀንም፤ የስልክ ቃለመጠይቅ ይደረግልሻል። ዳኘው፤ ግዚያዊ የመከላከል ትእዛዝ ከሰጠሽ፤ እንደ አንድ የዚህ ትእዛዝ አካል መጠን፤ ግፍ ፈጻሚው ወድያውኑ ቤቱን ለቆ እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል።

**ይህንን በታ ለቅቄ መውጣት አለብኝ ምክንያቱም ግፍ ፈጻሚው የት እንደምኖር አሁን አውቋል። ያደረኩትን የቤት ኪራይ ውል ማፍረስ እችላለሁን?**

አዎን። የቤተዘመድ ግፍ ሰለባ ከሆኑ ውል ማፍረስ ይችላሉ። ለአከራዮ የጽሁፍ ማስታወቅያ መስጠት አለቦት ከዚህም ጋር ከፍርድ ቤት ያገኙትን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ቅጂ ወይም እውቅናና ተቀባይነት ካለው ሶስተኛ አካል (ለምሳሌ ፖሊስ፣ የጤና ባለሙያ፣ ወይም የዲሲ የግፉ ደህነንት ባለስልጣን ወይም አማካሪ) የሰጥዎትን ዶኩመንቶች ቅጂ አክለው ይስጡ።) ውሉ፡ የጽሁፍ ማስታወቅያዎን በሰጡ በአስራ አራተኛው **(14)** ቀን ይፈርሳል።

**በዚህ የወረርሽን በሽታ ወቅት፡ ግፍ ፈጻሚዬ ከቤት አስወጣሻለሁ እያለ እያስፈራራኝ ነው። የምሄድበት ቦታ የለኝም። የቤት ኪራይ በመክፈል ረገድ እየተጋገዝኩ የነበርኩ ብሆንም፤ የቤት ኪራይ ውል ውስጥ የለሁም። ከቤት ሊያስወጣኝ ይችላልን?**

ምናልባት። ይህ የሚሞረከዘው እርስዎ የቤቱን ኪራይ በመክፈል ረገድ፤ በመኖርያ ቤቱ የመኖር መብት ያሎት እንደ አነስተኛ ተካራይ (subtenant) ይቆጠራሉ ወይም አይቆጠሩም የሚለው ላይ ነው። እንደ አነስተኛ ተከራይ የሚቆጠሩት በአንዳንድ ሁኔታዎችዎ ይመረኮዛል፤ ለምሳሌ ከግፍ ፈጻሚዎ ጋር መጀመርያ ሲገቡ የደረሳችሁበት ስምምነት ምን እንደነበር፤እንዲሁም ግፍ ፈጻሚዎ ከቤቱ እንዲወጣ በፍርድ ቤት ታዟል ወይስ አልታዘዘም የሚለው ነጥብ ላይ ይመረኮዛል። ጉዳዮን በተለይ የሚመለከት ምክር ለማግኘት ወደ **ሊጋል ኤድ** (Legal Aid's tenant hotline) በስልክ ቁጥር **(202) 628-1161** ይደውሉ ወይም አገልግሎታችንን ለማግኘትና ስለጉዳዮ ምክር ለማግኘት በኦንላይን ያመልክቱ

**ግፍ ፈጻሚዬ የሴክሽን ስምንት (Section 8) ቤቶችን ለማግኘት ኩፖን አለው። እኔም በኩፖኑ ውስጥ አለሁ።ግን የቤቱ የበላይ ሃላፊ (Head of Household) አይደለሁም። ከሱ ጋር ለመገላገል ስወስን ኩፖኑን ልጠቀምበት እችላለሁን?**

ምናልባት። ይህ የሚሞረከዘው በጉዳዮ ሁኔታ ላይ ነው። በስልክ ቁጥር (**202) 535-1000** በመደወል ወድያውኑ ከ **ዲ-ሲ-ኤች-ኤ** (DCHA) ጋር ተገናኝተው፡ (1) በኩፖኑ ውስጥ

እንዳሉ (2) የቤተዘመድ ግፍ ሰለባ መሆንዎን (3) ግ ጠይቋቸው። ለዚህም ጉዳዮን በተለይ የሚመለከት ምክር ለማግኘት በስልክ ቁጥር (**202) 628 1161** ወደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid**)** ይደውሉ።

## <u>ህዝባዊ ጠቀሜታዎች</u>

**ግፍ ፈጻሚዬ ለቤተሰባችን ገንዘባዊ እርዳታ የሚያድረግ ነበር። እኔ ግን ከዛ ሁኔታ መላቀቅ ስለነበረብኝ ወጣሁ። በዚህ በወረርሽኝ ግዜ፤ ለምግብና ለአንዳንድ ቁሳቁሶች መግዥያ ላገኘው የምችል እርዳታ አለን?**

ለ SNAP ጠቀሜታዎች (ብዙ ጊዜ ፉድ ስታምፕ ተብሎ ይጠራል) እና ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ (Temporary Assistance for Needy Families) (በአጭሩ ታንፍ (TANF) ) ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ቲ-ኤ-ኤን ኤፍ TANF) ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች፤ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆችና ለነፍሰ ጡሮች የጥሬ ገንዘብ እርዳታ ይሰጣል።

ኦንላይን ማመልከት ይችላሉ፣ የዲሲ አክሰስ ሞባይለ አፕ( DC Access mobile app) ተጠቀሙ። ማመልከቻዎን ፋክስ አድርጉ፤ (ማመልከቻዎች በ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተዋል) ፤ ማማልከቻዎችዎን ካዘጋጁ በኋላ ከታች አድራሻቸው ወደ ተጻፉት የአገልግሎት ጣብያዎች (ቁጥራቸው ከታች አለ) ሊልኳቸው ወይም በአካል ሊሰጡ ይችላሉ ነገር ግን በአሁኑ ግዜ፤ ለጤንነት ጥበቃ ሲባል፤ በአካል መገኘት አይበረታታም።

ኮንግሬስ ሃይትስ የአገልግሎት ማእከል
(Congress Heights Service Center)
4049 South Capitol St., SW
ስልክ ቁጥር: (202) 645-4546
ፋክስ: 202-654-4524

ኤች ስትሪት የአገልግሎት ማእከል
( H Street Service Center)
645 H St. NE
የስልክ ቁጥር: (202) 698-4350

ፋክስ: 202-724-8964

ቴለር ስትሪት የአገልግሎት ማእከል
(Taylor Street Service Center)
1207 Taylor St. NW
የስልክ ቁጥር: (202) 576-8000
ፋክስ: 202-576-8740

በተጨማሪም **ፓንዴሚክ-ኢቢቲ፣ ወይም ፒ-ኢቢቲ (Pandemic-EBT፣ ወይም P-EBT)** የሚባል አዲስ ፕሮግራም አለ። ከ COVID-19 ጋር በተያያዘ የትምህርት ቤቶች መዘጋት ምክንያት ነፃ የትምህርት ቤት ምግቦች ማግኘት ላልቻሉ ቤተሰቦች ተጨማሪ የሆነ የምግብ ድጋፍ ይሰጣል። ዲ ኤች ኤስ (DHS) ለቤተሰቦች ዌብሳይት( website )ና P-EBT የጥሪ ማዕከል ፈጥሯል፣ በስልክ ቁጥር 202-868-6663 ይደውሉ።

## የስናፕ SNAP ና ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ጠቀሚታዬን ለማግኘት ምን ያህል ግዜ መጠበቅ አለብኝ?

የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ፤ የስናፕ (SNAP) ማመልከቻዎን ለማጥናት 30 ቀናት ይፈጅበታል። ግን ለተቻኮለ የምግብ እርዳታ ብቁ ሆነው ከተገኙበተቀላጠፈ መንገድ ይደረግሎታል። ምክንያቱም 1) በየወሩ $100ና ከ $150 በታች የወር ገቢ ስላሎት 2) ለቤት ኪራይና ለመብራት፣ውሃና ጋዝ በየወሩ የሚከፍሉት ወጪ በየወሩ ከሚያገኙት ገቢ ስለሚበልጥ። በነዚህም ምክንያቶች የምታደርጉት ማመልከቻ በሰባት ቀናት ውስጥ መልስ ያገኛል።

የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ፤ በአብዛኛው ለ ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ማመልከቻዎች በ 45 ቀናት ውስጥ ነው መልስ የሚሰጠው።

ለስናፕና ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ያስገቧቸው ማመልከቻዎች አንዴ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ፤ የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል፤ በፖስታ ጠቀሜታዎን ወይም ገንዘቦን የሚቀበሉበት ካርድ (Electronic Benefits Transfer (ወይም EBT) ይልክሎታል። ከዛ በኋላ ካርዶን እያስገቡ የሚፈልጉትን መግዛት ይችላሉ።

## የስናፕ SNAP ወይም የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ጠቀሜታዎችን ለማግኘት በማመልከት ረገድ ችግር ካጋጠመኝ የት ነው የምደውለው?

በስልክ ቁጥር (202) 727-535 ማህበራዊ ጉዳይ  ክፍል( Department of Human Services) መደወል አለበት። መስመር ካጡ  ወይም ገና እርዳታ የሚያስፈልጎት ከሆነ፤ በስልክ ቁጥር (202) 628-1161ወደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) መደወል አለቦ ወይም አገልግሎት ለማግኘት በ online በመግባት ያመልክቱ።

## በኔ ላይ ግፍ የሚሰራው ሰው፤ ለችግረኛ ቤተሰቦች በሚሰጠው እርዳታ በ ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ም ሆነ በማገኘው የምግብ ኩፖን (food stamps) እንደ አንድ የቤተሰቤ አባል ተመዝግቧል።ይህንን ሰው እንዴት አድርጌ ነው ከዚህ የማስወጣው ?

እርስዎ፤ እንደ አንድ የቤተሰቡ የበላይ አካል እርስዎ የተመዘገቡት፤ ለዲ-ኤች-ኤስ (DHS) የአገልግሎት
ማእከል ይህንን ሰው አስወጡልኝ የሚል ደብዳቤ በመጻፍ፤ ወረቀቶችዎ እንዲስተካከል ማድረግ ይችላሉ። ግን ሌላው ሰው ከሆነ፤ ሁለታችሁም በጋራ የየግላችሁን እርዳታ እንድታገኙ የጋራ ማመልከቻ ለዲ-ኤች-ኤስ (DHS) ማስገባት አለባችሁ።

## የጤና ዋስትና ኢንሹራንስ ያስፈልገኛል በዚህ በ ወረርሽኝ አደጋ ወቅት እንዴት ነው ኢንሹራንስ የማገኘው?

በገቢዎ መጠንና እና በኢሚግሬሽን ባሎት ወረቀት የሚመረኮዙ ጥቂት የተለያዩ አማራጮች አለዎት።

**ሜዲኬድ** (Medicaid) ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና የአሜሪካ ዜጋ የሆኑ አካለስንኩላን፤ ህጋዊ በአሜሪካን አገር ህጋዊ ወረቀት ያላቸው ወይም ሌሎች ህጋዊ ወረቀት ያላቸው፤ የህክምና አገልግሎት እንድያገኙ የሚከፍልላቸው ነው። (ስለሜዲኬድ ገቢ መቆረጥ ከታች ይመልከቱ) ሜዲኬድ ላይ ለማመልከት፤ ኦንላይን ላይ DC Health Link የሚል ውስጥ ገብተው ማመልከቻ ይሙሉ ወይም የሞሉትን ማመልከቻ Application ወደ ሚከተለው አድራሻ ይላኩ:

ዲሲ ሄልት ሊንክ (DC Health Link)
Department of Human Services
Case Records Management Unit
P.O. Box 91560
Washington DC 20090

በተጨማሪም ማመልከቻው በአማርኛ፣በ ስፓኒሽ ቋንቋ፣ በቻይናና  በፈረንሳይኛ ቋንቋ ይገኛል።

**አሊያንስ** (Alliance) እና **የስደተኞች ልጆች ፕሮግራም** (Immigrant Children's Program) ለአዋቂዎች (አሊያንስ) እና ለህጻናት (የስደተኖች ልጆች ፕሮግራም) የሜዲኬድ የስደተኛ አቋምን ሳይሆን የሚዴኬድ የገቢ መስፈርቶችን ለሚያሞሉ የጤና እንሹራንስ ሽፋን ይሰጣሉ። ለዚህ የሚሞላው ማመልከቻ ለ ስናፕ (SNA) ና ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) የሚሞላው ዓይነት ነው። ፎርሙን በ ኦንላይን መሙላት ይቻላል፣ የዲሲ አክሰስ ሞባይል አፕን( DC Access mobile app) ይጠቀሙ። በእንግሊዘኛ፣ በ ስፓኒሽ እና በ አማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን ማመልከቻ ከሞሉ በኋላ  (ቁጥሩ ከወደታች ወደ ተጻፈው) የአገልግሎት ማእከል  በፋክስ መላክ፣ ወይም በአካል ሂዶ ማመልከቻውን መስጠት ይቻላል፤ ነገር ግን ይህ በአሁኑ ወቅት፤ በበሽታ እና ደህንነት ምክንያት፤ በአካል ቀርቦ ማመልከት አይበረታታም።

ኮንግሬስ ሃይትስ የአገልግሎት ማእከል
(Congress Heights Service Cente)
4049 South Capitol St., SW
ስልክ: (202) 645-4546
ፋክስ: 202-654-4524

ኤች ስትሪት የአገልግሎት ማእከል
(H Street Service Center)
645 H St. NE
ስልክ: (202) 698-4350
ፋክስ: 202-724-8964

ቴለር ስትሪት የአገልግሎት ማእከል
(Taylor Street Service Center)
1207 Taylor St. NW
ስልክ: (202) 576-8000
ፋክስ: 202-576-8740

ስለህዝባዊ ጠቀሜታዎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሎት፤ የሚከተለውን ጽሑፍ በኦንላይን ይመልከቱ፤ Legal Aid's Frequently Asked Questions About Public Benefits in the District. ህዝባዊ ጠቀሜታን በሚመለከት እርዳታ ካስፈለግዎ፤ በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161 ወደ ሊጋል ኤድ** ይደውሉ ወይም online አመልክቱ።

**<u>የገብያተኞች ጥበቃ/መከላከያ (</u>**Consumer Protection)

**ግፍ ፈጻሚዬ በኔ ስም የብድር ካርድ አውጥቷል። ይህንን እሱ የወሰደውን ብድር እምድከፍል ተከስሼአለሁ (ወይም ብድሩን እንድከፈል ውሳኔ ተላልፎብኛል) ። ዕዳ ሰብሳቢዎች ለማበረታቻ ተብሎ ከመንግስት የሚሰጠኝን ክፍያ ሊወስዱ ይችላሉን?**

በአጠቃላይ አነጋገር መልሱ አይችሉም ነው። እነኚህ አዲሶቹ የማበረታቻ ክፍያዎች፤ አበዳሪዎች ወይም ዕዳ ሰብሳቢዎች፤ ሊወስዷቸው አይችሉም። በግብር አስከፋዮች፣ በተማሪዎች የትምህርት ብድር ሰጪዎች፤ወይም ባልተከፈሉ የልጅ አሳዳጊ ክፍያዎች ሊነጠቁ አይችሉም፡፤

በዚህ ባለንበት የወረርሽኝ ወቅት፤ የመንግስትና የዲስትሪክቱ ህጎች፡ ገበያተኞችን ለመጠበቅ አያሌ  ድጋፍ ሰጪ ህጎችን አውጥተዋል። ይሄን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሎት Legal Aid's Frequently Asked Questions About Debt Collection Protections የሚለውን ጽሁፍ ይመለከቱ። ከቤተዘመድ ሁካታ ጋር የተያያዘ የዕዳ ክፍያ ክርክር ካለቦትና እርዳታ ካስፈለጎት፤ ከሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀነ-ቀጠሮዎ በፊት ከ**ሊጋል ኤድ (**Legal Aid) ጋር በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161** ተገናኙ።

**<u>ከመንግስት የሚሰጥ የማበረታቻ ክፍያ</u>**

### ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች አሉኝ። ሆኖም ለልጆች የሚሰጥ ተጨማሪ የማበረታቻ ክፍያ አላገኘሁም ለምን?

ይህ ሊሆን የሚችልበት ቢያንስ ሶስት ምክንያቶች አሉ፣

- ግብር ለመክፈል ፎርም ሲያስገቡ ምናልባት ልጆችዎን እንደ ጥገኞችዎ አላስገቧቸውም ሊሆን ይችላል።ወይም
- እርሶ ልጆችዎን እንደ ጥገኞችዎ ለማስገባት ዕድል ከማግኘትዎ በፊት ሌላኛው ወላጅ ተሯሩጦ እንደ ጥገኞቹ አስገብቷቸው ሊሆን ይችላል።
- ከመንግስት ማለትም ከሶሻል ሴኩሪቲ (Social Security) ወይም ከ ኤሰኤስ=ዲአይ (SSDI)፣ ኤሰኤስ አይ (SSI)፣ ቬርጂኒያ( VA)ወይም የባቡር ጡረተኞች ( Railroad Retirement አባል ስለሆኑ)ክፍያዎችዎን የሚያገኙት በቀጥታ ወደ እርሶ ጋ በመላክ ስለሆነ፤ በአይ አር ኤስ መዝገብ ውስጥ ልጆቹ የእርሶ ጥገኞች መሆናቸውን ስላላስመዝገቧቸው ሊሆን ይችላል።

  ስለዚህ በግብር መክፈያ ፎርም ውስጥ ልጆቹ የኔ ጥገኞች ናቸው ብሎ ያስመዝገበ ወላጅ፤ለእያንዳንዱ ልጅ የሚሰጠውን የማበረታቻ ክፍያ ያገኛል ማለት ነው።

  በማንኛውም እንዲህ በመሰለ ወቅት፤ ተጨማሪውን የማበረጽቻ ክፍያውን፤ ሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት (Recovery Rebate Credit) የተባለውን ከ2020 ግብር ፎርም ጋር በመሙላት ሊያገኙ ይችላሉ።

### የትኛው ወላጅ ነው ልጆቹ የኔ ናቸው ብሎ የመጠየቅ ህጋዊ መብት ያለው ?

ልጆቹ ከግማሽ አመት ለበለጠ ግዜ አብረውት የሚቀመጡ ወላጅ ነው ልጆቹን በግብር ፎርሙ ውስጥ ጥገኞቼ ናቸው ብሎ በየአመቱ በአያሬስ ፎርም(IRS Form 8332) ለማስገባት ህጋዊ መብት ያለው።

## **እንደ አንድ ልጆቹ ከእርሱ ጋር እንደሚኖሩ ወላጅ፤ ለልጆች ተብሎ የሚሰጠውን ተጨማሪ ምክፍያ ለማግኘት እችላለሁን**

**ምናልባት**፡ ለልጆቻቸው የሚሰጠውን የአንደኛውንም ሆነ ሁለተኛውን ዙር ተጨማሪ የማበረታቻ ክፍያ ያላገኙ፤ ልጆቻቸው ከእነሱ ጋር የሚቀመጡ ልጅ አሳዳጊ ወላጆች፤ ሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት( The Recovery Rebate Credit) የሚባለውን ከ2020 ግብር ፎርማቸው ጋር በማስገባት ሊያገኙ ይችላሉ። ይሁንና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሁለት አስፈላጊ ነገሮች አሉ፤

- ይህ ሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት( Recovery Rebate Credit) የሚሰጠው በ 2020. የነበሩትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።
    - ስለዚህ ለአቅመ አዳም ያልደረሰው ልጅዎ በ 2019 ከእርሶ ጋር የሚኖር በ 2020 ግን ከእርሶ ጋር የማይኖር ከሆነ (ምንም እንኳን ባለፈው አመት የልጆችዎን የማበረታቻ ክፍያ ያላገኙ ቢሆኑም) ይህንን ሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት( The Recovery Rebate Credit), ማግኘት አትችሉም።

○ በተመሳሳይም፤ ሌላ ሰው በ2019 የግብር መክፈያ ፋይሉ ውስጥ፤ ልጆቹ የኔ ጥገኞች ናቸው ብሎ ካስመዝገባቸውና እርሶ ምንም ባያገኙም እና ልጅዎ ደግሞ በ 2020 እድሜው አስራ ሰባት አመት ከሞላው (ማለትም ልጅዎ ብቁ ስለማይሆን) ይህንን ሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት( Recovery Rebate Credi)የሚባለውን ለማግኘት ብቁ አይሆኑም።

- ጥገኛ ልጆችዎ በ2020 ከእርስዎ ጋር ቢኖሩም እንኳን፤ እርሶ እድል ከማግኘትዎ በፊት፤ ሌላው ወላጅ ጥገኞቼ ናቸው ብሎ ካስገባቸው፤ የልጆች ተጨማሪ የማበረታቻ ክፍያውን ሊያገኙ አይችሉም።
- በኦንላይን በ2020 የግብር መክፈያ ፎርሙ ላይ ልጆቹን እንደ ጥገኞች ቢያስገቧቸውም፡ አስቀድሞ ሌላ ሰው ጥገኞቼ ናቸው ካለ፡ እርሶ ያስገቡት ውድቅ ይሆናል። በዛን ወቅት በወረቀት ፋይል ማድረግ አለቦት።

- እንዲህ ሲያደርጉ ደግሞ አይ አር ኤስ (IRS ) ጉዳዩን በበለጠ እንዲመለከተውና የትትኛው ወላጅ ነው በ2020.ክፍያው የሚገባው ብሎ ጠለቅ ብሎ እንዲያጠናው ይገፋፋዋል ማለት ነው። እንዲህ አይነቱ ጥናት ሲደረግ ደግሞ እርሶ ልጆችዎ ከግማX አመት በላይ ከእርሶ ጋር እንደነበሩ የሚያረጋግጡ መረጃዎችን ሁሉ ሰብስበው መቆየት አለቦት፡፡ የእነዚህ ማረጋገጫዎች ዝርዝር በIRS Form 886-H-DEP. ይገኛል፡፡

- አይ አር ኤስ (IRS ) አንዴ የወረቀት ፎርም ካስገቡ በኋላ ከስንት ግዜ በኋላ መልስ እንደሚሰጦት የሚያስረዳ መረጃ የለንም፡፡

**በእኔ ላይ ግፍ የፈጸመው ግለሰብ፤ ለልጅ ማሳደግያ ይከፍለኝ የነበረውን ክፍያ መክፈል ስላቋረጠ ያልተከፈለ የቀድሞ ክፍያ አለበት። ስለዚህ ይሄ ከመንግስት ለማበረታቻ ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ ለእሱ ከሚሰጠው በሙሉ ነው ማግኘት የሚገባኝ ወይስ በከፊል?**

ሲኤሴስዲ (CSSD)፤ የኬርስ( CARES Act) ውል ተብሎ በሚታወቀው ህግ መሰረት ወይም ከሪካቨሪ ሪቤት ክሬዲት (Recovery Rebate Credit )ግብር ለመክፈል ሲሞሉ አብሮ ከሚሞላው  ና ከመጋቢት 2020 የማበረታቻ ክፍያ፤ ልጆቹ ከእርሱ ጋር ከማይኖሩ ወላጅ የተወሰደውን ክፍያ ይሰበስባል፡፡

ከታህሳስ 2020 ጀምሮ እስከ መጋቢት ድረስ  መንግስት የከፈለው እርዳታ እንደ የልጆች ክፍያ ተደረጎ መወሰድ አይችልም።

መንግስት  ከ መጋቢት 2020  የማበረታቻ ክፍያ ገንዘብ የሚቆርጠው፤  የሚከፈላቸው ሰዎች እንደሚከተሉት ሲሆኑ ብቻ ነው፤

- ልጆች ከ እርሱ ወይም ከ እርስዋ ጋር የማይቀመጡ ወላጅ ሆኖ፤ ልጆቹ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ተቀባዮች ሲሆኑ ወይም ልጆቹ ከሌሎች ጋር በፎስተር ኬር የሚያድጉ ከሆነ (foster care) ፤ቢያንስ ለአንድ ልጅ ከሚሰጠው ገንዘብ *$150* የሚያህለውን ገንዘብ ካልሰጠ ይቆረጥበታል።

- ልጆች ከ እርሱ ወይም ከ እርስዋ ጋር የማይቀመጡ ወላጅ፤ለአንድ ልጅ እስከ *$500 የሚደርስ* ገንዘብ ባለዕዳ ከሆነና ልጆቹ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) የገንዘብ እርዳታ ተቀባይ እስካልሆኑ ድረስና በፎስተር ኬር ውስጥ የሌሉ እስከሆኑ ድረስ፤ገንዘብ እተተቆረጠ ይሰጣል።

የተቆረጠው ገንዘብ የልጅ አሳዳጊነት መብት ላለውና መከፈል ለሚገባው ወላጅ ይሰጣል።

- ልጆቹ በፎስተር ኬር የሚኖሩ ካልሆነ ወይም መንግስት ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጠው እርዳታ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ተቀባይ ሆነው ፍጹም የማያውቁ ከሆነ ፤ የማበረታቻቸው ገንዘብ ልጆቹ አብረው ለሚኖሩት ወላጅ ይሰጣል።
- በተለይ ልጆቹ በፎስተር ኬር (foster care) ውስጥ ወይም ቲ--ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) በመባል የሚታወቀው መንግስት ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚያደርገው የገንዘብ እርዳታ ተቀባይ ከሆኑ፤ ከማበረታቻ ክፍያ የተቆረጠው ገንዝብ፤ ቢያንስ አነስተኛ ክፍሉ ወደ ዲስትሪክቱ ገቢ ይሆናል።

ከመንግስት ስለሚሰጥ የማበረታቻ ክፍያ ተጨማሪ ጥያቄ ካሎት፤ [Legal Aid's Frequently Asked Questions About How to Get and Protect Your Stimulus Payment]. የተሰኘውን የሊጋል ኤድን የጥያቄና መልስ ጽሁፍ ተመልከቱ። የማበረታቻ ክፍያው እንዴት እንደሆነ ለመረዳት፡ ከግብር መሙላት ጋር እንዴት እንደተያያዘ በደንብ ለማወቅ (ከአያሬስ ጋር እንዴት እንደሚመዘገቡ ለማወቅ እርዳታ ካስፈለጎት የገንዘብ እርዳታ ኔትዎርክ ([Financial Stability Network)] የተባለውን ይመልከቱ።

## <u>**ወንጀላዊ**</u>

### በላዬ ላይ ወንጀል የፈጸመው ግለሰብ በአሁኑ ወቅት በ እስር ላይ ይገኛል። አሁን የኮቪድ አደጋ ባለበት ወቅት ይፈታ ይሆን?

አዎን ሊፈታ ይችላል። በዚህ በያዝነው የወረርሽኝ በሽታ ወቅት የእስርቤቶች ክፍል አንዳንድ ቀለልያለ ወንጀል የፈጸሙ ማለትም ህግ የመተላለፍ ጥፋት የፈጸሙ፤ የቤተዘመድ ሁከት

ያደረሱ ሰዎችን ለመፍታት የራሱን ውሳኔ ማድረግ ይችላል ። እስርኞች የት ቦታ እንዳሉ ለማወቅም ሆነ የመፈታት ዕድላቸው ምን እንደሆነ ለማየት በኦንላይን vinelink.com የተባለውን መጎብኘት ይችላሉ ። በተጨማሪም የአሜሪካን ጠበቃ ጽህፈት ቤት (**United States Attorney's Office)** ጋ በ ስልክ ቁጥር (**202) 252-1900** በመደወል የእስረኞቹ የመለቀቅ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ጠበቃውን ሊጠይቁ ይችላሉ።

**በእኔ ላይ ግፍ የፈጸመው ግለሰብ፤ የተሰጠኝን የሲቪል መከላከያ ትእዛዝ ስለጣሰ፤ ክስ ማቅረብ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**

ግፍ የፈጸመቦ ሰው የተሰጦትን የሲቪል መከለከያ ትእዛዝ( Civil Protection Order) ከጣሰ ሁለት መንገዶች አሉ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችልዎት፤

- ጉዳዩ በመካሄድ ላይ እያለ ፖሊስ ይጥሩ። ልክ እንደማንኛውም ሌላ ወንጄል፤ ፖሊሶቹ ምርመራቸውን ያካሂዳሉ። ተገቢ ከመሰላቸው መጥርያ ይሰጣሉ።

- የትእዛዝ መጣስ ክስ (Motion for Contempt) ያቅርቡ። የትእዛዝ መጣስ ክስ ወደ ኦንላይን www.probono.net/dccourts በመግባት  ወይም ፎርሞቹን ከ DVD@dcsc.gov በማውጣት ማመልከቻዎን ያጠናቅቁ። የትእዛዝ መጣስ ክሱን (Motion for Contempt)  ለመሙላት እርዳታ ካስፈለጎት በመጀመርያ በስልክ ቁጥር **(202) 879-0157 በመደወል ወይም ከ ዲሲ ሴፍ ጋር ፡ የስለባዎች መስመር D.C. Victim Hotline at 1-844-4HELPDC (1-844-443-5732) Domestic Violence Clerk's Office at (202) 879-0157** ወይም ከዲሲ ሴፍ (D.C. SAFE) ጋር ለመገናኘት ይደውሉ  የማንቋሸሽ ክስ ጥያቄዎች (Motions for Contempt) እየታዩት ያሉት በዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ (D.C. Office of the Attorney General) በሚገኙ ጠበቃዎች ነው፣ እና ተገቢ ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ ክስ ይመሰርታሉ።

## <u>ስደተኛነት/ኢሚግሬሽን (Immigration)</u>

**ስደተኛ ልጄን በመወከል፤ የወጣት ስደተኞች ልዩ ሁኔታ ማህበር (Special Immigrant Juvenile Status (SIJS) ውስጥ እየተሳተፍኩ ነው። ታድያ ልጄ በቅርቡ አስራ ስምንት ዓመት ስለሚሞላው ከማህበሩ መውጣት አለበት። ይህንን በተመለከተ በዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠን ቀጠሮ አሁንም ይከበርልናል?**

የዲሲ ላይኛው ፍርድ ቤት( DC Superior Court) ለእንዲህ አይነቶች ችሎቶች ቀጠሮ ሊስጥ ይችላል።ለዚህም ልጅዎ አስራ ስምንት አመት ከመሙላቱ በፊት እንዲያግዞ ከጠበቃ ጋር  ተነጋገሩ።

ከስደተኞች ጋር የተዛመደ ጥያቄ ቢኖሮት ዘወትር የሚጠየቁ የሊጋል ኤድ የጥያቄና መልስ ጽሁፍን  Legal Aid's Frequently Asked Questions About Immigration During the COVID-19 Health Emergency ይመልከቱ ወይም ሊጋል ኤድን በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161 ደውለው ያናግሩ ወይም ኦንላይን** online **ይግቡና አገልግሎታቸውን ለማግኘት ይጠይቁ።**

***

ጉዳዮን በተመለከተ ህጋዊ ምክር ለማግኘት ከፈለጉ ከሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር ተገናኙ።የኖርትዌስትና የሳውት ኢስት (Northwest and Southeast) መስርያ ቤቶቻችን በአሁኑ ወቅት ለህዝብ ዝግ ቢሆኑም በስልክና በኦንላይን ክፍት ነን አገልግሎታችንን ከፈለጉ በስልክ ቁጥር (**202) 628-1161** ወይም በኦንላይን online ያመልክቱ።